# የጌታ በዓል

ከሃብተሥላሴ ደኛቸው

በቤተ ክርስቲያናችን የዘመናት አቆጣጠር ከዓመቱ ክፍላት አውራኅ አንዱ መጸው ነው ። ይህም ከመስከረም ፳፮ —ታኅሣሥ ፳፭ ያለው የሦስት ወራት (የ፺ ቀኖች) ጊዜ ነው ። ዓመቱን በየሦስት ወራት ጊዜ ከአራት የሚከፍሉት እያንዳንዳቸው የዓመቱ ክፍላተ አውራኅ የየራሳቸው የሆነ የአየር ጠባይና መልካዓ ምድራዊ የተፈጥሮ ገጽታ አላቸው ። መጸው የቡቃያ የዘር የአበባ ፣ የእሸትና የመጐምራትና የመጠውለግ ጊዜ ሲሆን በጋ (ሐጋይ) የሙቀትና የአዝመራ መሰብሰቢያ ፣ ፀደይ የበልግና የጉልጓሎ ክረምት የዝናም የእርሻና የዘር ክፍለ ጊዜ ነው ። አሁን ያለንበት ፀደይ የዝናቡ የጭቃው የእርሻውና የዘሩ ጊዜ አልፎ ምድር በልምላሜ ጸጋ ተውጣ በስነ ጽጌያት አሸብርቃ በፀሐይ ብርሃን ደምቃ የምትታይበት ጊዜ ነው ። ጥቅምት ወርሃ ጽጌም ይባላል ።

ከዚሁ አንጻር በዚሁ ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወት የሚታሰበው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የንጽህት እናቱ የቅድስት ድንግል ማርያም ስደት ነው ።

በመሬት ላይ የወደቀ ዘር አዲስ አካል ገዝቶ በመብቀል ፍሬ እስከሚያፈራና ለመኸር እስከሚደርስ መሞት መፍረስና መበስበስ አለበት ፍሬው የሚገኘው በመሬት የተለያዩ ችግሮች ከታለፉ በኋላ ነው ።

ጥፋቱ ባስከተለው የቅጣት ፍርድ ልዩ ልዩ ጸዋትዎ መከራ መቀበል መሰደድና መሞት የነበረበትን የሰው ልጅ ለማዳን ሰው የሆነውና በሥጋ ከይሲ (እባብ) ተሠውሮ ሰውን ለጥፋት የደረገውን ሰይጣን በተጠቀመበት ጥበብ በሰው ሥጋ አድሮ ድል ለመንሳት ሥጋ የለበሰው የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግል ማህጸን ካደረበት ጊዜ አንስቶ እስከ ዕለተ ስቅለቱ ልዩ ልዩ መከራ ተቀብሏል ። በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ወርኃ ጽጌ ጥቅምት ኅዳር የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ከዕለተ ልደቱ እስከ ዕለተ ስቅለቱ (ሞቱ) ለሰው ልጆች ሕይወትና ነፃነት ፣ሰላምና ደኅንነት የተቀበለባቸውን ፀዋትዎ መከራ የምናስብበት ጊዜ ነው ። ከስደት ፣ እሥራትና መንገላታት በኋላ የደኅንነት ፍሬ (መኸር) የተገኘው በሞቱ ነውና ። (ኤፌ. ፪፥፲፮)

በነዚህ ወራት ሕፃኑ ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ከቤተ ልሔም ወደምድረ ግብጽ ተሰደዋል ። ስለስደቱ የሚነገሩ ብዙ ምክንያቶች ሲኖሩ ፤ ምሥጢሩ ጠለቅ ያለ ትርጉም ያዘለ ነው ።

በኦሪቱ፡-“ . . .በአንተና በሴቲቱ በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል ፣ አንተ ሰኰናውን ትነክሳለህ” (ዘፍ.፫፥፲፭)

ተብሎ እንደተጻፈው የተነገረው ትንቢት ሲደረስ የተቆጠረው ሱባዔ ሲፈጸም ከድንግል የተወለደው የሔዋን (የሴቲቱ) ዘር የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የዲያብሎስን ሥራ ለማፍረስ የተንኮል አሽክላውን ለመበጣጠስና ራሱን ለመቀጥቀጥ እንደተገለጠ ባወቀ ጊዜ ዲያብሎስ በመስቀል ላይ ድል እስከሚመታ የሴቲቱን ዘር ሸኰና ለመንከስ ብዙ ጥረት አድርጓል ። ለሕፃኑ ስደት ከሚሰጡት ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው ። የኢየሱስ ስደት ጊዜው ደርሶ በመስቀል ላይ እስኪሞት ከወዲሁ የሚደርሱትን የሰይጣን ወጥመዶች ለማለፍ ጊዜው ሳይደርስ እንዳይሞትና ለጊዜው አስፈላጊ ካልሆነ ሞት ለመሰወር ፣የሰይጣን መንፈስ ለቁጣ (ለጥፋት) ካነሳሳው የወቅቱ ሰው ከሄሮድስ ጭካኔ ለመሸሽ ነው ። ሄሮድስም ለሰይጣን መንገድ በመስጠት ለቁጣና ለጥፋት የተነነሳሳው ያለምክንያት አልነበረም ። ሥልጣኑን የሚቀናቀን ፈታኝ ትንቢት ተናንቆት ነው

“ አንቺ ቤተ ልሔም የይሁዳ ምድር
ከይሁዳ ገዥዎች ብትበልጭ
እንጂ አታንሽም ሕዝቤን እሥራኤልን የሚጠብቅ መስፍን
ከአንቺ ይወጣልና” (ሚክ. ፭-፪)


የሚለው ትንቢት በቤተ ልሔም አካባቢ መፈጸሙ በተሰማ ጊዜ የታወከውና የተሸበረው የሄሮድስ ኅሊና ብቻ አልነበረም ተባባሪዎቹንና መላይቱን ኢየሩሳሌም አስደንግጧል ፣ አሸብሯል ። “ የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው ? ” እያሉየምሥራቅ ነገ

ሥታት ለእውነተኛው ሰማያዊ ንጉሥ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሊገብሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሠራዊት አስከትለው ሕፃኑ ወደተወለደበት (ቤተ. ልሔም) መጓዛቸውንም ለተወለደው ንጉሥ ማረጋገጫ ስለሆነ በገዥነት ሥልጣን ላይ የነበረው ሄሮድስን የዋጠው የጭንቀት ማዕበል ሙቀቱ ምን ያህል እንደነበረ መገመት አያስቸግርም ።

ሌላው “ ልጄን ከግብጽ (ወደ ግብጽ) ጠራሁት” ተብሎ በነቢዩ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው ። ሆሴዕ ፲፩፡፩

እነዚህን ትንቢቶች የሚያገሉ ምሱ ብዙ ምሳሌዎችም ነበሩ ። “ ልጄን ከግብጽ ጠራሁት ” የተባለው ለጊዜው ለያዕቆብ ሲሆን ፤ የትንቢቱ ፍጻሜ ለእምላክ ያዕቆብ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረ ነበር ። ሌሎችም አበው ከጌታ በፊት በልዩ ልዩ ምክንያቶች ወደ ግብጽ ተሰደዋል ። ያንኑ የአበውን ፈለግ ለመከተልና በግብር ለመፈጸምም ነው ። ከነዚህም ሁሉ ጋር ክህደትና አምልኮ ባዕድ የሠፈነበትን ምድረ ግብጽ ከጣኦት አምልኮ ማጽዳት (ማላቀቅ) ዋነኛው የጌታ ፈቃድ ስለነበር ከስደቱ ምክንያቶች አንዱ መሆኑ ተመልክቶአል ። አዳም በልጅነት ክብር ሰባት ዓመት ሕጉን ጠብቆ ከኖረበትና ሞት ሳይኖር በየሺህ ዘመኑ እየታደሰ እንዲኖር ከተፈጠረበት ተድላ ገነት ወጥቶ የተሰደደው ስደት የተካሰው በጌታ ስደት ነው ። በጌታ ስደት አጋንንት ከሰዎች ልቡና ወጥተው ተሰደዋል ። ሀገርን ጥሎ መሰደድ ሰማዕትነት ነውና ጌታችን የሰማዕታትን ስደት በስደቱ ባርኮ አርአያነቱን አስተምሮበታል ። ትናትም ሆነ ዛሬ “ከዚህኛው አገር ቢያሳድዱችሁ ወደሌላይቱ ሂዱ ፤ የእግዚአብሔር ሀገር ሠፊ ነውና ” የተባለውም ትምህርት ከዚህ የስደት ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው ።

ዮሴፍ በሕፃኑ ኢየሱስ ሕይወት ፊት ተደቅኖ የነበረውን አደጋ ፤ ከችግሩም ለማምለጥ መደረግ የነበረበት ዘዴ ምን እንደነበረ አላወቀም ነበር ። ማንም ሰው ይሁን የመሰለ የተፈጥሮ ድካም አለው ።ሁላችን በሕይወታችን የሚደርሰውን ችግር እናውቅም የሕይወት ባለቤት ፈጣሪ ግን




ማእምረ ኅቡአት ስለሆነ መንገዱም ዘዴውም አለው ።“ የተወለደውየአይሁድ ንጉሥ የት እንደተወለደ አይታችሁ ተመልሳችሁ ንገሩኝ እኔም እንደናንተ ሂጄ እንድሰግድለት ፤ በሚል ተንኮል የተሸኙት የምሥራቅ ነገሥታት (ሰብአ ሰገል) በሄደበት መንገድ እንዳይመለሱ ገልጾላቸው ። በሌላ መንገድ ወደ የሀገራቸው ተመለሱ ፤ ዮሴፍ ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ ግብጽ እንዲሰደድ በመልአክ በሕልም ተነገረው በሌሊት ተነስቶ ተጓዘ በስደትም በመከራም ከኢየሱስ አልተለዩም ። አብረውት የኖሩ ናቸው ። ልደቱ በእንስሳት በረት ፤ ሕፃንነቱ በበረሃ ስደት ተደምሮ መከራው የተፈጸመው በመስቀል ነው ። ራስን መጠበቅ ሕይወትን ለማዳን ጥረት ማድረግ የፍጡራን የተፈጥሮ ሕግ ነው ። እግዚአብሔርየሥነ ፍጥረቱን ሕይወት ይመለከታል ፤ ይመራል ፤ ይጠብቃል ፤ከሚደርሰውም ችግር ያድናል ። ለዮሴፍ

የተነገረው ከጠላት ማምለጫው ብቻ አልነበረም በስደት ሀገር የሚቆይበትም ጊዜ ጭምር ነበር ። “ ሳልነግርህ እንዳትመለስ ” እዎ ከችግር ለመዳን በሕይወት ለመኖር የሚሰጠውን መለኮታዊ ትምህርት መቀበልና ሕጉንና ትእዛዙን መጠበቅ ያስፈልጋል ።

ጉዞው ለሕፃኑም ሆነ ለእናቱ እጅግ አስቸጋሪ ከባድም ነበር ።በለጋ ሕይወት ያልጠነከረ ሰውነት በጨለማ በበረሀ በረሀብና በውሃ ጥም እየተቀጡ በሥጋትና በጭንቀት ተውጦ መሰደድ እጅግ ይከብዳል ዮሴፍ ለተጠራበት ሰማያዊ ድምጽና በሕልም ለተገለጸለት መመሪያ ታዛዥ ነበር ። አልዋለም ፤አላደረም አልዘነጋም አላመነታም ፤ ጉዞ የጀመረው ወዲያው ነው ። ሕልሙን ያየበት ሌሊቱን እስኪነጋ እንኳ አልጠበቀም በሌሊቱ በጨለማው ተነስቶ ከጌታ ጋር ጉዞውን ቀጠለ ። አብርሃም ከቤተሰቡና ከዘመዶቹ ተለይቶ እንዲወጣ በተጠራ ጊዜ ወደማያውቀው አገር አምኖ ሄደ ። ጥሪውን ሰምተው ትእዛዙን ያከበሩ ብዙዎች ናቸው ። ከዘመድና ከቤተሰብ መለየት ከተወለዱበት አገር መሰደድ በባዕድ ምድር ባዕድ ሆኖ መኖር አስቸጋሪነቱ ቢታወቅም ጥሪውን ተቀብሎ ከጌታ ጋር መጓዝ ሰማዕትነት ነው ። የጌታችን ስደት ለሰማዕታት ስደት መሠረቱ ነው የተባለውም ለዚህ ነው ። ከዓለም ተሰደው መስቀሉን በመሸከም እስከ ቀራንዮ የተከተሉት ብዙዎች ናቸው ።

በቤተ ልሔም ለተወለደው የአይሁድ ንጉሥ የሚገባውን ግብርና እጅ መንሻ ይዘው የመጡ የምሥራቅ ነገሥታት የሄሮድስ የሸፍጥ አደራ ሳይጠብቁ በሌላ መንገድ ወደ ሀገራቸው መመለስ ፤ ዮሴፍ ከመልአክ በተገለጸለት መሠረት እናቱንና ሕፃኑን ኢየሱስን ይዞ በሌሊት መሰደድ ፤ ሄሮድስን እጅግ ስላስቆጣው በመቶ ሺህ ለሚቆጠሩ ሕፃናት እልቂትና ዋይታ መንስዔ ሆኖአል ። በቁጣው ፻፵፬ ሺህ ሕፃናት አልቀዋል ። ከአንድ ዓመት ተኩል እስከ ሁለት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሁሉ በመዓቱ ወላፈን ተገርፈዋል ። ተሠውተዋል ።

ሄሮድስ የጥፋት እቅዱና ፍላ
ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል

ጐቱ እንዳይሰት በሕፃኑ ዕድሜ
ግምት ሁለት ዓመት የሆናቸውንና
ከዚያም ያነሱትን አስፈጅቷል ። የመ
ጨረሻ ጭካኔና ሰይጣናዊ ሥራ ነበር ።
ሕፃንን ከእናት ጡት ነጥሎ እንደ
ጎመን በሠይፍ (በሰለት) መቁረጥ።
ለወገኑ ሕይወት የማይሳሳ የሰው ልጆች
ጠባይ ምን ይሆን ? ይህ ደም ለሕፃናቱ
ና ፣ ለመላውም የሰው ዘር ሁሉ ደሙን
ሳፈሰሰው ቸር አምላክ የቀረበ የንጹ
ሐን (የሰማዕትነት ) ደም ነው ። በእ
ውነት ፈራጅ ጌታ ዙፋን ፊት የሚ
ከስ ፣ የሚበቀልና የሚያስፈርድ ደም ።
በነቢዩ ኤርምያስ ትንቢት ተገልጾ
በጊዜው ተፈጽሞ የነበረው በሄሮድስ
ጊዜ ተደግሞ በነዚህ ሕፃናት ደምና
ዋይታ ወደአርያም ያረገው እንባ ከቤተ
ልሔም እስከ ራማ አስተጋብቷል ።
የአምላክን የፍትሕ በር አንኳኩቷል ።
ዛሬም ቢሆን አመጽ የተመላበት
ዓለም ከዚያ ዓይነቱ ግፍና ሰቀቀን
እምብዛም አልጠራም ዋይታና ሃዘን
በራሄልና በሄሮድስ ዘመን ብቻ አላከ
ተመም ። በይቀጥላል ተወርሶአል ።

ግብፅ ለጊዜው የስደት መጠለያ
እንጂ መኖሪያ አልነበረችም። የጠፋው
ተገኝቶ ፣ የተሰደደው ተመልሶ
ተስተካክሏል ። ለኛም ይህ ዓለም ሀገ
ራችን ይህም ምድር ቤታችን አይደ
ለም ። የምንኖርበት ሌላ አገር ሌላ
ዓለም አለ ። ተስፋ የምናደርገው የም
ንጠብቀው ያንን ነው ። (፪ ቆሮ፡፭፡፩)

በጌታ ስም የፈሰሰው የንጹሐን
ሕፃናት ደም አፍሳሹን ማጥፋቱ የማ
ይቀር ነው ። ሄሮድስ በከፉ አሟሟት
ሞተ ።የከፉና በደለኛ ሰው እድሜ
ወትሮም ረጅም አይደለም ፣ ሕይወ
ቱም ፍርሀት ፣ ጸጸት ፣ ሥጋትና ጭን
ቀት የተመላ ስለሆነ ህልውናው የቅጠል
( የወረቀት) አምድ ነው ። ዘመኑም
እንደጥላ ነው ። (ኅጥእን )ኃጢአተኛን
ሰው እንደ ደጋ ዛፍ ከፍ ክፍ ብሎ
አየሁት በተመለስኩ ጊዜ ግን የነበረ
በትን ሥፍራውን አጣሁት ” ተብሏል
አማሟቱም ከፉና የሚያስጠላ ነው ።

ጌታችን ሊያድናቸው መጣ ሊያድና
ቸው የመጣውን ግን አልተቀበሉትም
መድኃኒታቸውን ጠሉ ፣ በልደቱ መላእ
ክት ዘመሩለት ሰዎች ግን በንጹሐን
ሕፃናት ደምና በወላጆች ሐዘን ነው
የተቀበሉት ።

“እኔ እስከምነግርህ በዚያው ቆይ”
ተብሎ በመልአክ እግዚአብሔር
በተነገረው መሠረት ዮሴፍ ከሕፃኑ
ኢየሱስና ከእናቱ ድንግል ማርያም
ጋር ሄሮዶስ እስኪሞት በግብፅ ኖረ
“ የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና
ተነሳ ሕፃኑን እናቱንም ይዘህ ወደ
እሥራኤል አገር ተመለስ ”እግዚአብ
ሔር ስራውን የሚሰራባቸው ጊዜአት
አሉት በእምነትና በቅንነት መጠ
በቁ መልካም ነው። የያዙትን መተው
የተነገሩትን መርሳት ይጐዳል ሁሉም
ጊዜውን ጠብቀው ከስደት ተመለሱ ።
ከባይተዋርነት ኑሮ ተላቀቁ ኅዳር ፮
ቀን በያመቱ የሚከበረው ጌታችንና
እመቤታችን ከስደት የተመለሱበት
ቀን መታሰቢያ ስለሆነ ነው ።

ደብረ ቁስቋም

እመቤታችን ድንግል ማርያም
ሕፃኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ፣ ዮሴፍንና
ሰሎሜ ከስደት ሲመለሱ የአረፉበት
ቦታ ናት ጌታ ከቅድሳት እናቱና
ከመንፈሳውያን አገልጋዮቹ ጋር ያረፈ
በት የባረከትና ያከበራት በመሆኑ
መታሰቢያነቷ እንዳይጠፋ ቤተ ክርስ
ቲያን እንዲሰራባት መስዋዕት እንዲሰ
ዋባትና የእግዚአብሔር ስም እንዲ
መስገንባት ተደርጓል ። ከደቀመዛሙ
ርቱና ከእናቱ ጋር ተገኝቶ ሥርዓተ
ቁርባን ፈጽሞባታል ።

ከዘመነ ሰማዕታት ጀምሮ ፩ሺ፱፻፲፪
ካህናት በደብረ ቁስቋም እየተገኙ
ቦታዋ በመንፈሳዊ ታሪኳ ተጠብቃ
እንድትኖር አድርገዋል ።
የቤተክርስቲያን አባቶች ቅዱስ ቴዎፍ
ሎስና ቅዱስ ቄርሎስ ሳይለዩ በኅዳር
፮ ቀን እየተገኙ ያከብሩ እንደነበር
ተጽፎአል ።

ቅዱስ ያሬድ “ ሊቀ ጳጳሳት
ቴዎፍሎስ በዚህ ቅዱስ ቦታ በተገኘሁ
ጊዜ በመንገድ ከአጋጠመኝ ድካም
ነፍሴ አረፍ አለ ፣ ከልጅዋ ከወዳጅዋ
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እመቤታችን
ቅድስት ማርያም ስለአረፈችበት”
ሲል ተናግሯል ።

ከዚህም ሌላ ጌታችን ኢየሱ
ክርስቶስ ከእመቤታችን ድንግል ማር
ያም ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋብ ያለ
መብልና ያለ መጠጥ አምስት ቀን
እንደቆዩ በቤተክርስቲያን የታሪክ
መጻሕፍት ተገልጾአል ።